

ለሰዎች አስብ

ሰዎች ዋጋ እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ። ለዚህ ነው ግለሰቦች የሌሎችን ትኩረት ለማግኘት ሲሉ የሆነ ዓይነት ባህሪ ሲያሳዩ የሚስተዋለው። ትኩረት እንዲሰጧቸው ወይም እንዲገረመባቸው በማሰብም የጀግኖቻቸውን ተረቶች ወይም ታሪኮች ሊፈጥሩ ይችላሉ።

አንድ ደከሞት ከስራ ወደ ቤቱ የሚገባን ሰው እንመልከት። ወደ ሳሎን ሲገባ አራቱም ልጆቹ ብቻቸውን ተቀምጠዋል። የመጀመሪያ ልጁ አስራ አንድ ዓመቱ ሲሆን ቴሌቪዥን ያያል። ሁለተኛው ልጅ ራቱን እየበላ ነው። ሶስተኛው በአሻንጉሊቶቹ ይጫወታል። አራተኛው የቤት ስራውን ይሰራል። አባት ድምፁን ከፍ አድርጎ "አሰላሙ አለይኩም" አላቸው። አንደኛው ልጅ ቴሌቭዥን ላይ በሚያየው ነገር ተመስጧል። ሁለተኛው ልጅ ፀጥ ብሎ ራቱን ይበላል። ሶስተኛው ከአሻንጉሊቶቹ መለያየት አልቻለም። አራተኛው ልጅ አባቱን ሲያይ መፅሐፎቹን ወርውሮ በደስታ ወደ አባቱ ሮጠ። እጁን ሳመውና ወደ መፅሐፉቱ ተመለሰ። ከአራቱ ልጆች በአባቱ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ የሚሆነው የትኛው ነው? ምላሻችን ተመሳሳይ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። አራተኛው ልጅ ነው። ቆንጆ ስለሆነ አይደለም። ጎበዝም ስለሆነ አይደለም። ለአባቱ ዋጋ ስለሰጠ ብቻ።

አንድ ሰው ለሌሎች በተጨነቀ ቁጥር እነሱም ለሱ ያላቸው ፍቅርና ክብር ይጨምራል። ከፍጥረታት ሁሉ የበላይ የሆኑት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሰዎች ላይ እነዚህን ነጥቦች ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ነበር። ሰዎች ጭንቀታቸው የነብዩ ጭንቀት ችግራቸው የነብዩ ችግር ነው ብለው እንዲያስቡ ያደርጉ ነበር።

አንድ ቀን ኹጥባ ለማድረግ ወደሚንበራቸው እየወጡ ሳለ አንድ ሰው ወደ መስጊድ ገባ።

የአላህ መልዕከተኛ! አለና ስለኃይማኖቱ ይጠይቃቸው ጀመር። ብዙ እውቀት አልነበረውምና። ነብዩ ሲመለከቱት ኹጥባው እስኪያልቅ ድረስ ሊታገስ የማይችል ገጠሬ ነው። ድጋሚም መስጊድ ላይመጣ ይችላል። ጉዳዩ ለሰውዬው በጣም አንገብጋቢ ነው። ለዚህም ነው ኹጥባውን አቋርጠ ጥያቄ የጠየቃቸው። ነብዩ የሚያስቡት ከራሳቸው አንፃር ሳይሆን ከሰዎች አንፃር ነው። ከተከበረው ሚንበራቸው በመውረድ ወንበር እንዲመጣላቸው አዘዙና ከሰውዬው ፊት ለፊት ተቀመጡ። ከዚያም እስኪገባው ድረስ ለጥያቄው መልስ ሰጡት። ኹጥባቸውን

ለመጨረስ ወደ ሚንበራቸው ተመለሱ። ምንኛ ታላቅ ሰው ነበሩ። ምንኛ መሰልቸት ያማያውቁ ሰው ነበሩ። ባልደረቦቻቸውንም በዚሁ ስላሰለጠኗቸው ለሰዎች ይጨነቁ ነበር። ለሰዎች ጥሩ አቀባበል ነበራቸው። ደስታና ሀዘናቸውን አብረው ይካፈሉ ነበር።

ጦለሃ ለካዕብ (ረ.ዐ) እንዴት እንደሆነለት እንይ። ከዕብ ኢብኑ ማሊክ (ረ.ዐ) እድሜው ከገፋ፣ አጥንቶቹ ከደከሙና አይኑ ከጠፋ በኋላ ነብዩ ለመጨረሻ ጊዜ በተሳተፉበት የተቡክ ጦርነት ላይ ወደ ኋላ በመቅረቱ የተከሰተውን የማይርረሳ የወጣትነት ትዝታውን ያጫውተናል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህዝቡ ለጦርነት እንዲዘጋጅ ጥሪ አቀረቡ። የሠራዊቱ ቁጥር ሰላሳ ሺ እስኪደርስ ድረስ ሰዎችን ያሰባስባሉ። ይህ የሆነው ፍራፍሬዎች በበሰሉበት፣ ጥላ በሚናፈቅበትና የበረሃው መቀት በበረታበት ወቅት ነበር። ጉዞው ረጂም ጠላትም ሀያልና አደገኛ ነበር። ብዙ ሰዎች የተመዘገቡ ቢሆንም የጥቂት መሰሊሞች ሰም በመዝገቡ ላይ አልሰፈረም።

ከዕብ እንዲህ ይላል፡- በወቅቱ በጣም ሀብታም ነበርኩ። ሁለት በቅሎዎች ነበሩኝ። ጠንካራም ነኝ። ነገ ገበያ ሄጄ ለጦርነቱ የሚሆን ነገር እገዛና ወደ ጦሩ እቀላቀላለሁ አልኩ። በሚቀጥለው ቀን ወደ ገበያ ሄድኩ። የሆነ ጉዳይ አጋጠመኝና ሳልገዛ ተመለስኩ። ኢንሻ አላህ ነገ ገዛዝቼ እሄዳለሁ አልኩ። አሁንም ቀረሁ። ልቤ ወደ ጣፋጮቹ ፍራፍሬዎችና ወደ ጥላው አዘነበለ። በመጨረሻ ጥለውኝ ሄዱ። ወደ ገበያ ሰሄድና ከተማ ውስጥ ስዘዋወር በንፍቅና የተጠረጠሩ ወይም አላህ ወደ ጦርነት እንዳይሄዱ የፈቀደላቸውን ሰዎች ብቻ ነው የማገኘው። ከዕብ መዲና ውስጥ ቀረ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሰላሳ ሺ ባልደረቦቻቸው ጋር ተቡክ ደረሱ። በአቀባህ ውል ላይ ከተገኙ ሰዎች መካከል የቀሩ ሰዎች ካሉ ለማጣራት ይቃኙ ጀመር። ከዚያም "ከዕብ ኢብኑ ማሊክ የታለ?" በማለት ጠየቁ። አንድ ሰው "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሁለቱ ካባዎቹ ከለከሉት። ቤቱን በኩራት እየጠበቀ ነው" ሲል መልስ ሰጣቸው። መዓዝ ኢብኑ ጀበል "ምን ዓይነት መጥፎ ንግግር ነው የምትናገረው? ወላሂ የአላህ መልዕክተኛ! ከሱ ላይ ጥሩን እንጂ መጥፎ ነገር አይቼ አላውቅም" አለ። የአላህ መልዕክተኛ ዝም አሉ። ከዕብ ቀጠለ፡- "ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጦርነቱን ጨርሰው ወደ መዲና ለመመለስ ሲዘጋጁ ማሰብ ጀመርኩ። ከዚህ መጥፎ ከስተት ራሴን እንዴት ነው የማድነው? ከቤተሰቦቼ መካከል ምክር ይሰጡኛል የምላቸውን ሰዎች ሁሉ አማክራለሁ። እውነቱን ከመናገር ውጪ ሌላ የሚያድነኝ ነገር እንደሌለም ተረዳሁ።"

ነብዩ መዲና እንደደረሱ መስጊድ ገብተው ሁለት ረከዓ ሶላት ከሰገዱ በኋላ ቁጭ ብለዋል። ከጦርነቱ የቀሩ ሰማንያ ያህል ሰዎች እየመጡ ከጦርነቱ የቀሩበትን ምክንያት በማቅረብ ይቅርታ ጠየቁ። ነብዩም የውሰጣቸውን ሚስጥር ለአላህ በመተው ይቅርታቸውን ተቀበሏቸው። ከዕብ ኢብኑ ማሊክ መጣ። ሰላምታ አቀረበ። ነብዩ ሲያዩት ሳቁ። የቁጣ ሳቅ። ከዕብ ከፊት ለፊታቸው ተቀመጠ። ነብዩም

"ለምን ቀረህ? የምትጋልበው ነገር አልገዛህም?" አሉት። በእርግጥም የምጋልበው እንስሳ ገዝቻለሁ አለ። "ታዲያ ለምን ቀረህ?" አሉት። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሰዎችን የማሳመን ኃይል አለኝ። ለሌላ ሰው ቢሆን ኖሮ ምክንያት አቅርቤ ራሴን ከቅጣት እጠብቅ ነበር። ሆኖም እርስዎን ለማስደሰት ብዬ ብዋሽ አላህ በሌላ ነገር እንዲቆጡብኝ ሊያደርግ ይችላል። እውነቱን ከተናገርኩ እርስዎ ይናደዱብኛል። ሆኖም እውነቱን በመናገሬ አላህ ይቅርታ ያደርግልኛል። የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አቅሙም ጉልበቱም እያለኝ ነው ወደ ኋላ የቀረሁት" አለ። ነብዩም "እውነቱን ተናገረ" አሉና "ሂድ አላህ ባንተ ላይ ውሳኔ እስኪያስተላልፍ ድረስ ጠብቅ" አሉት። ከዕብ እግሮቹን እየጎተተ ከመስጊዱ ወጣ። የፀፀት ስሜት እየናጠውና ሀዘን እያንገላታው። አላህ ምን ዓይነት ውሳኔ ያስተላልፍብኝ ይሆን እያለ።

ጥቂት ሰዎች ተከትለውት ወጡና "ወላሂ ከዚህ በፊት ኃጢያት ስትሰራ አይተንህ አናውቅም። አንተ ገጣሚ ሆነህ ሳለ እንዴት እንደ ሌሎቹ ሰዎች የአላህ መልዕክተኛን ማሳመን አልቻልክም? የሆነ ምክንያት ብታቀርብ ኖሮ ደስ ብሏቸው ምህረት ይጠይቁልህ ነበር። አላህም ይምርህ ነበር" ይሉታል። ከዕብ እንዲህ ይላል፡- "ሰዎቹ በጣም ሲጎተጉቱኝ ተመልሼ ውሸቴን ነው ልላቸው አሰብኩ። ሆኖም እንደኔ አይነት መልስ የሰጠ ሰው አለ? ስል ጠየቅኳቸው። ሁለት ሰዎች አንተ የሰጠኸውን አይነት መልስ ሰጥተው ተመሳሳይ ትእዛዝ ተሰጥቷቸዋል አሉኝ። እነማን ናቸው? ስል ጠየቅኩ። ሙራራህ ኢብኑ ረቢዓና ሒላል ቢን ኡመያ ናቸው አሉኝ። እነዚህ ሰዎች በበድር ጦርነት ላይ የተሳተፉና እኔም እንደ አርአያ የምቆጥራቸው ደጋግ ሰዎች ናቸው። "ወላሂ ወደ ነብዩ ተመልሼ ቃሌን ማጠፍና ራሴን ማዋረድ አልፈልግም" አልኩ።

ከዚያም ውስጡ በሐዘን እንደተሰበረ ወደ ቤቱ ሄደ። ብዙም ሳይቆይ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዕብና ጓደኞቹን ማንም ሰው እንዳያናግራቸው ትዕዛዝ አስተላለፉ። ከዕብ ሲናገር "ከዚህ በኋላ ሰዎች ለእኛ ያላቸው አመለካከት ተቀየረ። አገለሉን። ማንም ሰው አያናግረንም። ሰዎች በሙሉ እንደማያውቁን ሆኑ። ግድግዳውና መሬቱ ሳይቀር እንደ ባይተዋር ቆጠረን። ሁለቱ ጓደኞቼ ቤታቸው ውስጥ ተቀምጠው ቀንና ሌሊት ያለቅሳሉ። ፊታቸውን ሰው አይቷቸው አያውቅም። ልክ እንደ መነኩሴ ራሳቸውን በኢባዳ ጠመዱ። እኔ ወጣት ነኝ። ከሶስታችንም ጠንካራው እኔ ነኝ። መስጊድ ሄጄ እሰግዳለሁ። ወደ ገበያ ቦታም እሄዳለሁ። ነገር ግን ማንም አያናግረኝም። መስጊድ ገብቼ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጠገብ እቀመጣለሁ። ሰላምታም አቀርብላቸዋለሁ። ለሰላምታዬ መልስ ይሰጡኛል ወይስ አይሰጡኝም ስል እጨነቃለሁ። ካጠገባቸው እሰግዳለሁ። ሰረቅ አድርጌ እመለከታቸዋለሁ። ሶላት ላይ በምሆንበት ጊዜ ያዩኛል። ጨርሼ ሳያቸው ፊታቸውን ያዞራሉ።"

ቀናት እየጨመሩ በሄዱ ቁጥር ሰቆቃውም ጨመረ። ከዕብ በህዝቦቹ መካከል የተከበረና ዝነኛ ገጣሚ ነበር። ንጉሶችና ንግስቶች ያውቁታል። ግጥሞቹ በታላላቆች

ዘንድ የሚታወቁ በመሆናቸው ብዙ ሰዎች ሊያዩት ይናፍቃሉ። ሆኖም አሁን ቢድፍን መዲና የሚያናግረው ሰው ጠፍቷል። ማናገር ቀርቶ በአይኑ የሚያየው ሰው የለም። አሳዛኙ ከስተት አስፈሪ ነው። መገለሉ እጅግ በጣም ይፈታተናል። ሌላ ፈተና ተጨመረ።

አንድ ቀን ከዕብ በገበያ ቦታ እየተዘዋወረ ሳለ አንድ ሶሪያዊ ክርስቲያን "የከዕብ ኢብኑ ማሊክን ቤት የሚያሳየኝ ማነው?" ሲል ጠየቀ። ሰዎች ወደ ወደሱ አመለከቱት። ከገሳን ንጉስ የተላከ ደብዳቤም ሰጠው። ይገርማል። ከገሳን ንጉስ! ዜናው ሶሪያ ደርሷል ማለት ነው። የጋሳኒቲዎች ንጉስ ለሱ ተጨንቋል። እንዴት ይደንቃል! ለመሆኑ ከሱ ምን ነበር የሚፈልገው? ከዕብ ደብዳቤውን ከፍቶ አነበበው። "ከዕብ ኢብኑ ማሊክ ሆይ! ባልደረባህ እንዳገለለህ ሰምተናል። ከጥፋትና ከውርደት አገር መኖር የለብህም። ስለዚህ ወደኛ ና እንረዳሃለን" ይላል። ደብዳቤውን አንብቦ ሲጨርስ "ኢና ሊላህ! ካፊሮች እኔን ፍለጋ መጡ። ይህ በእርግጥም ትልቅ ፈተናና መከራ ነው" አለና ደብዳቤውን በፍጥነት በእሳት አቃጠለው። የንጉሱን ጥሪ ከቁብ አልቆጠረውም። አዎ በአንድ በኩል የንጉሶች ቤተ መንግስትና ቪላ በሮች ተከፍተው በጉጉት ይጠብቁታል። በዚህ በኩል ደግሞ የራሱ የመዲና ሰዎች ጠልተውታል። ሰላምታ ያቀርብላቸዋል። ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። መልስ አይሰጡትም። ይሁንና ይህ ነገር ፊቱን ወደ ካፊሮቹ እንዲያዞር አላደረገውም። ሰይጣን ሊያሸንፈውና የፍላጎቱ ባሪያ ሊያደርገው አልቻለም። ደብዳቤውን በእሳት አጋዬው።

ከዕብ ብቸኝነቱ እንዳንገላታውና መገለሉ እንደከበደው ቀናት ወደ ወር ተቀየሩ። ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይቅርታ አላደረጉለትም። ይህን ጉዳይ የሚዳኝ ወህይም አልወረደም። በአርባ ቀኑ ከኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተላከ ሰው መጥቶ የከዕብን በር አንኳኳ። ከዕብ ለእርቅ የሚያቢቃ ነገር ይዞ መጥቷል በሚል ተስፋ በሩን ከፈተ። ሆኖም መልዕክቱ "ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሚስትህ እንድትርቅ አዘውሃል" የሚል ነበር። እሱም "ልፍታት ወይስ ምን ላድርግ?" ሲል ጠየቀ። "አትፍታት። ነገር ግን አትቅረባት" ተባለ። ለሚስቱም "አላህ በዚህ ጉዳይ ላይ ብይን እስኪሰጥ ድረስ ቤተሰቦችሽ ዘንድ ቆይ" አላት። ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን መልዕክት ለሁለቱ ሰዎች ላኩ። የሂላል ቢን ኡመያ ሚስት ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በመምጣት "ሂላል ደካማ ሽማግሌ ነው። እንዳገለግለው ይፍቀዱልኝ" ስትል ጠየቀቻቸው። እሳቸውም "እሺ ግን እንዳይቀርብሽ" አሏት። እሷም "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እሱ ምንም መንቀሳቀስ አይችልም። ድርጊቱ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በጣም አዝኖ ቀንና ሌሊት እያለቀሰ ነው ያለው" አለች።

ቀናት እየጨመሩ በሄዱ ቁጥርና መገለሉ እየበዛ ሲሄድ ከዕብ ኢማኑን እንደገና መፈተሽ ጀመረ።

ሙስሊሞችን ሊያናግር ይሞክራል። እነሱ ግን መልስ አይሰጡትም። ለአላህ

መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላምታ ያቀርባል። መልሳቸውን አያገኝም። ስለዚህ የት ይሂድ? ማንን ያማክር?

እንዲህ ይላል ከዕብ፡- "ችግሩ በጣም እየባሰብኝ ሲሄድ ወደ አቡ ቀታዳ ሄድኩ። በጣም የምወደው የአጎቴ ልጅ ነው። አትክልት ቦታው ላይ አገኘሁት። ገባሁና ሰላምታ ሰጠሁት። ወላሂ ሰላምታዬን አልመለሰልኝም። "አቡ ቀታዳ ሆይ! በአላህ ልለምንህ አላህንና ነብዩን እንደምወድ አታውቅም?" አልኩት። መልስ አልሰጠኝም። በድጋሚ "አቡ ቀታዳ አላህንና ነብዩን እንደምወድ አታውቅም?" አልኩት። አሁንም ዝም አለኝ። ለሶስተኛ ጊዜ "በአላህ ልለምንህ አላህንና መልክተኛውን እንደምወድ አታውቅም?" አልኩት። "አላህና ነብዩ ያውቃሉ" አለኝ።" የአጎቱ ልጅና የሚወደው ሰው የሱን ሙስሊም መሆንና አለመሆን መናገር የማይችልበት ደረጃ ላይ እንደደረሰ ሲያይ ከዕብ የሰማውን ነገር መቋቋም አቃተው። አይኖቹ በእንባ ተሞሉ። በአጥር ዘሎ ወደ ቤቱ በመሄድ በቤቱ ግድግዳዎች ተወሰኖ ከዚያ ከዚህ እያማተረ ቆዬ። አይዞህ የምትለው ሚስቱም አጠገቡ የለችም። የሚያማክረው ዘመድም የለውም።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እነዚህ ሰዎች እንዲገለሉ ካዘዙ ድፍን አምሳ ቀን ሆነ። በአምሳኛው ሌሊት ላይ አላህ የሶስቱን ሰዎች ፀፀት መቀበሉን የሚያመለክት ወህይ አወረደ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኡሙ ሰላማ ቤት ነበሩ። መሳጮቹን ምዕራፎች አነበቡ። ኡሙ ሰላማም "ለምን አስደሳቹን ዜና አሁኑኑ ለከዕብ ኡበኑ ማሊክ አንነግረውም?" ስትል ጠየቀቻቸው። "ሰዎች ተሰብስበው በመምጣት ቀሪውን ሌሊት እንዳትተኚ ያደርጉሻል" አሏት። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሱብሂ ሶላትን ከሰገዱ በኋላ አላህ የሶስቱን ሰዎች ተውበት መቀበሉን አወጁ። ሰዎች መልካሙን ዜና ሊነግሯቸው በፍጥነት ወደ እነ ከዕብ ሄዱ። ከዕብ እንዲህ ይላል፡- "የሱብሂን ሶላት የሰገድኩት በቤቴ ጣሪያ ላይ ነበር። አላህ በመፅሐፉ በገለፀው መልኩ ነበር የተቀመጥኩት። ነፍሴ ጭንቅንቅ ብላለች። ሰፊዋ መሬት ሳትቀር ለኔ በጣም ጠባብ ናት። በጣም የሚያስጨንቀኝ ነገር ደግሞ በዚህ ወቅት እኔ ብሞት የአላህ መልዕክተኛ የማይሰግዱብኝ መሆኑ እሳቸው ከሞቱ ደግሞ ማንም ሰው እስከ መጨረሻው የማያናግረኝ መሆኑና ሰሞትም የሚሰግድብኝ አለመኖሩ ነው።

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለሁ አንድ ሰው ሰልዓ ተራራ ላይ ሆኖ ከፍ ባለ ድምፅ "ከዕብ ኢብኑ ማሊክ ሆይ! እንኳን ደስ ያለህ!" ሲል ሰማሁት። በስተመጨረሻ ከአላህ ዘንድ እፎይታ መምጣቱን ተረዳሁና ሱጁድ ወረድኩ። አንድ ጋላቢ በፈረስ ወደኔ መጣ። ሌላኛው ደግሞ ከተራራ ጫፍ ላይ ሆኖ ይጣራል። ጥሪው ከፈረሰኛው ይልቅ ቀድሞ ተሰማኝ። ድምፁን የሰማሁት ሰው መጨረሻ ላይ መጥቶ መልካሙን ዜና ሲነግረኝ ሁለቱንም ልብሶቼን አውልቄ አለበስኩት። ወላሂ ሌላ ልብስ አልነበረኝም። ከሰዎች ሁለት ልብሶችን ተውሼ ለበስኩና ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሄድኩ። ሰዎች በቡድን በቡድን እየመጡ "ተውበትህ ተቀባይነት አገኘ። እንኳን ደስ

ያለህ" ይሉኛል።

መስጊድ ውስጥ ሰገባ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር ቁጭ ብለዋል። ወላሂ ከጦለህ ቢን ኡበይዱላህ በስተቀር ቆሞ የተቀበለኝ ሰው የለም። ተነስቶ አቅፎ ከሳመኝ በኋላ መልሶ ተቀመጠ። ወላሂ የጦለሃን ድርጊት መቼውንም አልረሳውም። ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሄድኩና ሰላም አልኳቸው። ፊታቸው በደስታ በርቷል። ነብዩ ሲደሰቱ ፊታቸው ልክ እንደ ጨረቃ ያበራል። "እናት ከወለደችህ እለት ጀምሮ ካሳለፍካቸው ቀናት ሁሉ በላጭ ለሆነው ቀን እንኳን አደረሰህ አሉኝ።" "ይህ ብስራት ከእርስዎ ነው ከአላህ?" ስል ጠየቅኳቸው። "ከአላህ ነው" አሉና አንቀጹን አነበቡ። ከፊት ለፊታቸው ተቀመጥኩና "የአላህ መልዕከተኛ ሆይ! አላህ ተውበቴን ስለተቀበለኝ ንብረቴን በሙሉ ለአላህና ለመልዕከተኛው በሰደቃ መልክ እሰጣለሁ" አልኳቸው። እሳቸውም "የተወሰነውን አስቀር። ይህ ላንተ የተሻለ ነው" አሉኝ። "የአላህ መልዕከተኛ ሆይ! አላህ ነጻ ያወጣኝ እውነት ስለተናገርኩ ነው። አላህ ተውበቴን ስለተቀበለኝ ምስጋናውን ለማድረስ በህይወት እስካለሁ ድረስ እውነትን እንጂ ላልናገር ለራሴ ቃል ገብቻለሁ" አልኳቸው። አዎ አላህ የከዕብንና የሁለት ጓደኞቹን ተውበት በመቀበል ቀጣዩን አንቀጽ አወረደ።

"በነብዩ በዚያም በችግሪቱ ጊዜያት /በተቡክ ዘመቻ/ ከነሱ የከፈሎቹ ልቦች /ለመቅረት/ ሊዘነበሉ ከተቃረቡ በኋላ በተከተሉት ስደተኞችና ረዳቶች ላይ አላህ በእርግጥ ፀፀታቸውን ተቀበለ። ከዚያም እነሱ ንስሃ መግባታቸውን ተቀበለ። እርሱ ለነሱ ሩህሩህ አዛኝ ነውና። በነዚያም በሶስቱ ሰዎች ላይ ምድር ከስፋትዋ ጋር በነሱ ላይ እስከጠበበች ነፍሶቻቻውም በርሳቸው ላይ እስከተጠበቡ ከአላህም ወደርሱ ቢሆን እንጂ ሌላ መጠጊያ አለመኖሩን እስካረጋገጡ ድረስ በቆዩት ላይ /አላህ ፀፀትን ተቀበለ።/ ከዚያም ይፀፀቱ ዘንድ ወደ ፀፀት መራቸው። አላህ እርሱ ፀፀትን ተቀባይ አዛኝ ነውና።"

እዚህ ታሪክ ላይ ትኩረት የምናደርግበት ነጥብ ጦለሃ (ረ.ዐ) ካዕብን ሲያየው ተነስቶ አቅፎ በመሳም እንኳን ደስ አለህ ማለቱ ነው። ካዕብ ለጦለሃ ያለው ኢድናቆት ከፍተኛ በመሆኑ ጦለሃ ከሞተ በኋላ ሳይቀር ከዕብ ይህንን ታሪክ እያወሳ "ወላሂ ጦለሃ ያደረገልኝን ነገር መቼም ቢሆን አልረሳውም" ይል ነበር። ጦለሃ የከዕብን ልብ ለመማረክ ምንድን ነው ያደረገው? ከሀሎቱን ተጠቅሞ ለሱ ያለውን ጭንቀት በማሳየትና ደስታውን በመካፈል በከዕብ ልብ ውስጥ ተደላድሎ ለመቀመጥ ቢቃ። ለሰዎች እዝነትንና ተቆርቋሪነትን ማሳየት ልባቸውን ያለመልመዋል። ጓደኛህ ፈተና ላይ ከሆነ "ፈተና እንዴት ነው ወላሂ በጣም ሳስብና ዱዓ ሳደርግልህ ነበር። ኢብራሂም ነኝ" ብለህ የጽሑፍ መልዕክት ብትልክለት ላንተ ያለው ክብር የማይጨምር ይመስልሃል? ያለ ምንም ጥርጥር ይጨምራል።

ጓደኛህ አባቱ ታሞበት ሆስፒታል ውስጥ በጭንቀት ተውጦ አባቱን እያስታመመ ከሆነ ደውለህ አባቱ እንዴት እንደሆኑ ከጠየቅከው በኋላ የማግዘህ

ነገር ካለ ንገረኝ? በፈለግከኝ ጊዜ ልረዳህ ዝግጁ ነኝ። በለው። በርግጠኝነት ያመሰግንሃል። ጢት ቢድጋሚ ደውለህ "ለቤተሰብ የሚያስፈልግ የሚገዛ ነገር ካለ እባክህ ንገረኝ?" በለው። ያመሰግንሃል። ዱዓ ያደርግልሃል። ላንተ ያለው ክብር ይጨምራል። እንዲህ ብሎ ከሚደውልለት ጓደኛው ጋር ራስህን አነፃፅረው። "ሄሎ ዛሬ ልንገዛና ወደ ባህር ዳር፣ ልንሄድ ነው። እንዴት ነው ከኛ ጋር መሄድ ትፈልጋለህ?" እሱም "አይ አባቴ በጣም ስለታመመ መሄድ አልችልም።" ዱዓ በማድረግና ስላሉበት ሁኔታ ባለመጠየቁ ይቅርታ በመጠየቅ ፋንታ "አውቃለሁ። እሳቸው ሆስፒታል ውስጥ አይደል እንዴ ያሉት። እናትህና እህቶችህ አጠገባቸው ካሉ በቂ ነው። አንተ ብዙም የምታደርግላቸው ነገር አይኖርም። ለማንኛውም ከፈለግክ ናና ተዝናንተህ አዕምሮህን አድስ ተመለስ" ብሎ ስልኩን ይዘጋል። ይህ ልጅ የጓደኛው አባት መታመም ምንም እንዳላሳሰበው ሆኖ ነው የቀረበው። ታዲያ ጓደኛው ለሱ የሚኖረው አመለካከት ምን ሊሆን ይችላል? ያለምንም ጥርጥር ለዚህ ጭንቀቱ ላላስጨነቀው ጓደኛው ያለው ክብር ይቀንሳል።

አንዴ ለጥቂት ቀናት ያህል ጅዳ ውስጥ ተቀምጬ አንድ መጥፎ ነገር ሊጋጥመኝ ነበር። ሰራ በጣም በዝቶብኝ ነበር። ወንድሜ "አላህ መፅናናቱን ይስጥህ። የአጎትህ ልጅ ጀርመን ውስጥ ሞቷል" የሚል መልዕክት ላከልኝ። የአጎታችን ልጅ ከሁለት ቀናት በፊት ነበር ለልብ ህክምና ወደ ጀርመን የሄደው። መርዶውን ወዳሰማኝ ወንድሜ ስደውል ሬሳው በቅርቡ ወደ ሪያድ እንደሚመጣ ነገረኝ። ዱዓ አድርጌና አላህ እንዲምረው ተመኝቼ ስልኩን ዘጋሁ። ከሁለት ቀናት በኋላ የጅዳው ስራዬ ተጠናቀቀ። ከዚያም ወደ ሪያድ ለመሄድ ጅዳ አየር ማረፊያ ሄድኩ። እዚያ ላይ የተወሰኑ ወጣቶች አገኘሁ። ሲያዩኝ አወቁኝና በየተራ ሰላም አሉኝ። ጥቂቶቹ ፀጉራቸውን ዘመን አመጣሽ ቁርጥ ተቆርጠዋል። እቀልዳቸው ጀመር።

በመሀል ስልክ ተደወለልኝ። አናግሬ ስጨርስ አንድ ወጣት መጥቶ ሰላም አለኝ። ሱፍና ሸሚዝ ለብሷል። ከዚያም "አለባበስህ በጣም ያምራል። ሙሽራ መስለሃል" አልኩት። ወጣቱ ለጥቂት ሴኮንዶች ዝም ካለ በኋላ "ያወቅከኝ አልመሰለኝም። እኔኮ የአከሌ ልጅ አከሌ ነኝ። ከጀርመን የአባቴን ሬሳ ይዤ መጥቼ አሁን ደግሞ ወደ ሪያድ ልሄድ ነው" አለኝ። በርሜል ሙሉ ቀዝቃዛ ውሃ በላዬ ላይ የተቸለሰብኝ ያህል ነው የተሰማኝ። እጅግ በጣም አዘንኩኝ። አባቱ ሞቶበት ሬሳ ይዞ መጥቷል። እኔ ደግሞ እቀልዳለሁ፤ እስቃለሁ። ይህ እጅግ በጣም አሳፋሪ ነገር ነው። "በጣም አዝናለሁ። ወላሂ አንተ መሆንህን አላወቅኩም። አላህ ፅናቱን ይስጥህ። አባትህንም አላህ ይማረው" አልኩት። ማንነቱን መለየት ቢያቅተኝ አይፈረድብኝም። ምክንያቱም ሁሌ የሚለብሰው ባህላዊውን ልብስ ጀለብያና ጥምጣም ነበር። ሱሪና ሸሚዝ ለብሶ ከወጣቶች ጋር ተሰብስቦ ጅዳ አየር ማረፊያ ውስጥ ሳገኘው እሱ መሆኑን በጭራሽ አላወቅኩም።

ለሌሎች መጨነቅ ማለት ስሜታቸውን መጋራት፣ ጭንቀታቸው ጭንቀትህ

መሆኑንና ደስታቸው ደስታህ መሆኑን መሳየት ነው። ለዚህ ነው ፕሮፌሽናል ካምፓኒዎች የህዝብ ግንኙነት ክፍል ያላቸው። የዚህ ክፍል ሚና ወቅታዊ ሠላምታዎችንና ስጦታዎችን ... ወዘተ መላክ ነው። አንድ ሰው ለሌሎች ዋጋ ከሰጣቸውና እንክብካቤ ካሳያቸው ልባቸውን ያገኛል። ይወዱታል። እዚህ ላይ ትክክለኛ የህይወት ምሳሌ እናገኛለን። አንድ ሰው በሰዎች በተሞላ ቤት ውስጥ ከገባና መቀመጫ ቦታ ካጣ አንድ ሰው ጠጋ ብሎ "ና እዚህ ጋ ተቀመጥ" ካለው ያ ሰው ለሱ ያለውን ጭንቀት አሳዬው። ይህ እንዲወደው ያደርገዋል። ወይም አንድ ሰው ራት ግብዣ ላይ ተገኝቶ ምግቡን ከያዘ በኋላ ባዶ ወንበር ሲፈልግ አንድ ሰው "ና እዚህ ጋ ተቀመጥ" ቢለው ለሰውዬው ያለውን ጭንቀት አሳዬው። ስለዚህ አንድ ሰው ለሰዎች ዋጋ ሲሰጥ ከነሱ ውዴታን ይቀበላል።

ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ለዚህ ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ይሰጡ ነበር። አንዴ ሚንበራቸው ላይ ተቀምጠው የጁሙዓ ኹጥባ ያደርጋሉ። አንድ ቤድዊን ገባና ወደሳቸው በመጠጋት ድምፁን ከፍ አድርጎ "የአላህ መልዕከተኛ ሆይ! እኔ ስለ ኃይማኖቴ ምንነት ምንም የማላውቅ ሰው ነኝ። እስቲ ስለኃይማኖቴ አስተምሩኝ" አላቸው። ከሚንበራቸው ወርደው ከሰውዬው አጠገብ ተቀመጡና እስኪገባው ድረስ አስተማሩት። ከዚያም ወደ ሚንበራቸው ተመለሱ። ይህ ለሰዎች ስለሚደረገው እንክብካቤ ታላቅ ማሳያ ነው። ማን ያውቃል ይህን ሰው ችላ ቢሉት ኖሮ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ ስለኃይማኖቱ ምንም ሳያውቅ ሊቀር ይችላል። ከአንድ ሰው ጋር በእጃቸው ሰላምታ ሲለዋወጡ ያኛው ሰው እጃቸውን ከመልቀቁ በፊት እሳቸው አይለቁትም ነበር። አንድ ሰው ሲያናግራቸው ፊታቸውን ወደዚያ ሰው ያዞሩ ነበር። ማለትም በሙሉ ትኩረት ያዳምጡት ዘንድ ፊታቸውንና አካላቸውን ወደሱ ያዞሩ ነበር።

ልምድ...

ልምድ እንደሚነግረን ሰዎች ዋጋ ከሰጠሃቸውና እንክብካቤ ካሳየሃቸው ልባቸውን ትይዛለህ። በነሱ ዘንድ ተወዳጅ ትሆናለህ።